# ወርሃዊ የአየር ጠባይ

# ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከጁን 1-30/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ እንዲሁም

## ከጁላይ 1-31/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጁላይ 2022
አዲስ አበባ

| ርዕስ | ገፅ |
|---|---|


እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ..... 3

ካርታ7. እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ..... 4

ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ..... 5

ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ..... 6

ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ..... 6

እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ..... 7

ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ..... 7

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ..... 7

እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ..... 8

ካርታ 11 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ..... 8

እ.ኤ.አ ከጁላይ1 እስከ 31/2022 የሚኖረው የአየር ..... 9

ጠባይ አዝማሚያ ..... 9

ካርታ 12 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 1-31, 2022 ዝናብ የማግኘት እድል ..... 10

..... 10

እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ..... 10

እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ..... 12


## እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

ባለፈዉ የጁን ወር ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ከዕለት ወደ ዕለት እየተጠናከሩ የመጡ ሲሆን፤ ዝናቡም ከደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች ጀምሮ ቀስ በቀስ ወደ ሰሜን፣ መካከለኛዉና የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየተስፋፋ በጁን መጨረሻዎቹ አስር ቀናት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎችን ያዳረሰና በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ እየተሻሻለ የመጣበት ሁኔታ ተስተዉሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ነጎድጓድ አዘልና በረዶ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በአጠቃላይ ባለፈዉ የጁን ወር በትግራይ፣ በአማራ፣ በምዕራብና መካከለኛዉ ኦሮሚያ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በሲዳማ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ደጋማና ምስራቅ ኢትዮጵያ፣ ሰሜን ሱማሌ፣ ሐረሪ፣ ድሬዳዋ እንዲሁም በአፋር ክልል ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ ዝናብ ከ 1- 4 ቀናት ያህል ከተመዘገበባቸዉ ጣቢያዎች መካከል አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል በደብረብርሃን 40.5፣ በሲሪንቃ 34.6፣ በአይከል 47.2፣ በነቀምቴ 135.0፣ 50.2፣ 43.8ና 48.6፣ በሊሙገነት 36.0ና 36.2፣ በበደሌ 51.3፣ 42.8ና 44.0፣በሳዉላ 30.5ና 30.3፣በጊምቢ 53.6ና 52.3፣ ፣ በአርጆ 38.5ና 64.5፣ በጎሬ 37.0፣ በነጆ 46.5ና 48.4፣ በአሶሳ 53.2፣ በዳንግላ 35.5፣ በአቦቦ 50.0፣ በላሬ 39.5ና 47.8፣ በማሻ 70.8፣ በአማን 53.7፣ በጋትራ 47.4፣ በአሶሳ 52.9፣ በፓዌ 38.4፣ በሻሁራ 42.6፣ በባህር ዳር 58.5፣ በዳንግላ 34.6 እና በሐረር 34.3 በሚ.ሜ.ይገኙበታል፡፡


ባለፈዉ የጁን ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም የትግራይ፣ የአማራ፣ የቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ የጋምቤላና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች ሁሉም ዞኖች፤ የአፋር ክልል ዞን 03፣ 05፣ 02ና 04፤ ሁሉም የወለጋና ሸዋ ዞኖች፣ የቡኖ በደሌ፣ የኢሉአባቦራ፣ የጂማ፣ የአርሲና ምዕራብ አርሲ እንዲሁም የምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ የጉራጌ፣ የስልጤ፣ የሀዲያ፣ ከምባታ ጠምባሮ፣ ሀላባና ወላይታ ዞኖች ላይ ከ50-438 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ10-29 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ የሲቲና ፋፈን፣ የደቡብ ኦሞ፣ የጌዴኦ፣ የኮንሶ፣ የቡረጂ፣ በጥቂት የባሌና ምስራቅ ባሌ፣ የጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ የአፋር ክልል ዞን 01 ላይም ከ25-50ሚ.ሜ የሚደርስ ከ10 ላነሱ ቀናት ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 7 እና 8)፡፡

ባለፈዉ የጁን ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በአፋር፣ በትግራይ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ እና በአማራ ሁሉም ዞኖች፣ በሁሉም የወለጋና ሸዋ ዞኖች፣ በቡኖ በደሌ፣ በኢሉ አባቦራ፣ በጂማ፣ በምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ በአርሲና ምዕራብ አርሲ እንዲሁም በጥቂት የባሌ በሲቲና ፋፈን፣ በጉራጌ፣ በስልጤ፣ በጥቂት የሀዲያ፣ ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ደረቃማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ ቆይተዋል (ካርታ 9) ፡፡


ካርታ 7.   እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 8   ኢ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 9   እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የጁን ወር ለክረምት ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ከዕለት ወደ ዕለት ተጠናክረው የተስተዋሉ ሲሆን፤ በሂደትም ከደቡብ ምዕራብ ወደ ተለያዩ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች በመስፋፋት አብዛኛውን ቦታ ያዳረሰና በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ እየተሻሻለ የመጣበት ሁኔታ እንደነበረ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተሰበሰቡና የተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በአንዳንድ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል። ይህም የተገኘው ዝናብ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻልም አልፎ ከጁን ጀምሮ የዘር ጊዜና የማሳ ዝግጅት በሚካሄድባቸው አካባቢዎች በወቅቱ ለመዝራት አመቺ ሁኔታ የነበረ ሲሆን፤ ቀደም ብለው ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኽር ሰብሎች በተሚላ ሁኔታ እንዲያድጉ የጎላ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአርብቶ አደርና በከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች የነበረው አነስተኛ የእርጥበት ሁኔታ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከባድ ዝናብ እንዲሁም ባሳለፍናቸው ቀናት በተከታታይ ዝናብ በማግኘት ላይ በነበሩ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት እና በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ለወንዝ መሙላትና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የጎርፍ መከሰት የነበረ ቢሆንም፤ በግብርናዉ እንቅስቃሴ ላይ ያደረሰዉ አሉታዊ ተፅዕኖ አልነበረም (ካርታ 10)፡፡


ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

በለፈው የጁን ወር የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በአብዛኛው በአባይ፣ ኦሞጊቤ፣ ባሮአኮቦ፣ በላይኛው እና በመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በላይኛው አዋሽ፣ ዋቢሸበሌ እና የላይኛዉ እና የታችኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው ናቸው፡፡በላይኛው ዋቢሸበሌ፣ ገናሌዳዋ፣ በታችኘው ስምጥሸለቆ እንዲሁም የመካከለኛው የላይኛዉ አዋሽ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ አርጥበት ሁኔታ እንደነበራቸው ተስተውሏል። የተቀሩት ተፋሰሶች ደረቅና ከፊል ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖ እንደነበር ተስተውሏል (ካርታ 11) ፡፡

ካርታ 11   እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# እ.ኤ.አ ከጁላይ1 እስከ 31/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ወር የክረምት ዝናብ በሁሉም የሀገሪቱ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ እየተስፋፋ እና እየተጠናከረ የሚሄድበት ጊዜ ከመሆኑም በላይ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ነጎድጓዳማና በረዶ አዘል ዝናብ ይከሰታል፡፡

በመጪው የጁላይ ወር ከደቡብ ንፍቀ ክበብ ወደ ሀገራችን እየገባ ያለዉ እርጥበት አዘል አየር እየተጠናከረ ሊሄድ እንደሚችልና ከዚህም ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል ወቅታዊውን ዝናብ በመደበኛ ሁኔታ ማግኘት የጀመሩትን የምዕራብ አጋማሽና የመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎችን ጨምሮ የሰሜን ምሥራቅ እና የምሥራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎችን የሸፈነ ዝናብ በተጠናከረ ሁኔታ ቀጣይነት እንደሚኖረዉ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም በተለይም ከወሩ አጋማሽ በኋላ ለተከታታይ ሰዓታት ያለማቋረጥ ዝናብ ሊዘንብ እንደሚችል እንድሁም በዉስን ሰዓት ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ሊኖር ይችላል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ተዳፋትና በወንዞች አካባቢ ለጎርፍ መከሰት መንስኤ ሊሆን ስለሚችል በማህበረሰባችንና የሚመለከተዉ ሁሉ ከወዲሁ አስፈላጊዉን ክትትልና ጥንቃቄ እንዲያደረግ እንመክራለን፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥለው ወር ላይ ከኦሮሚያ ጅማ  ኢሉአባቦራ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ በአዲስ አበባ፣ ከአማራ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፣ የሰሜን፣ የደቡብ፣ መካከለኛዉና ምዕራብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ አዊ ዞን፣ የዋግህምራ፣ ኦሮሚያ ልዩ ዞን፣ የሰሜን ሸዋ በተጨማሪም የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ የትግራይ፣ የአፋር፣ የጋምቤላና ከቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልል የመተከል ዞን፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የከፋ፣ የቤንች ሸኮ፣ ሸካና ምዕራብ ኦሞ የዳውሮ ልዩ ወረዳን ጨምሮ፣ ከደቡብ ብሄር ብሄረ ሰቦችና ህዝቦች ክልል የጉራጌ፣ የስልጤ፣ የሀዲያ፣ የሀላባ ጠምባሮ፣ ከምባታ፣ የወላይታ፣ የጋሞና ጎፋ በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም ከኦሮሚያ ክልል በቄለምና ምዕራብ ወለጋ፣ ምዕራብ እና ምሥራቅ ሐረርጌ፣ የአርሲና ምዕራብ አርሲ፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ ዞኖች፣ የሲዳማ ሁሉም ዞኖች እና ከሱማሌ ክልል ደግሞ የሲቲና ፋፈን ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ ያገኛሉ። በሌላ በኩል ቀሪዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች መጠነኛ የደመና ሽፋንና ደረቅ ሆነዉ ይቆያሉ(ካርታ 12)፡፡

ካርታ 12 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 1-31, 2022 ዝናብ የማግኘት እድል




## እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የጁላይ ወር የመኸር እርሻ እንቅስቃሴ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚከናወንበት ወቅት ሲሆን፤ በተለይም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች እርጥበት የሚስፋፋበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የዘር መዝራት ተግባራት በስፋት የሚከናወንበት ጊዜ ነው፡፡ እንዲሁም አስቀድመው በኤፕሪልና ሜይ ለተዘሩትና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙት የረጅም ጊዜ ሰብሎች ላሉበት ደረጃ የሚያስፈልጋቸውን ውኃ በቂ በሆነ መልኩ

የሚያገኙበት ጊዜ ሲሆን፤ በተጨማሪም እርጥበት አጠር የሆኑ አካባቢዎችም ውኃን ለማከማቸት መልካም አጋጣሚዎችን የሚያገኙበት ወቅት ነው፡፡ ከዚህም አልፎ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ አካባቢዎች ለሚከናወኑ የእንስሳት እርባታ የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ምቹ ሁኔታዎች የሚኖሩበት ጊዜ ነው፡፡

በሚቀጥለው የጁላይ ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች እየተጠናከሩ ሊሄዱ እንደሚችሉና ከዚህም ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል ወቅታዊውን ዝናብ በመደበኛ ሁኔታ ማግኘት የጀመሩትን የምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎችን ጨምሮ የሰሜን ምሥራቅ እና የምሥራቅ ኢትዮጲያ አካባቢዎችን የሸፈነና በአብዛኛው መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ እርጥበት እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ በተለይም የመኸር አብቃይ በሆኑትና ዘር መዝራት ባልተጀመረባቸው አካባቢዎች ለዘር ምቹ ሁኔታ እንደሚኖረዉ ይጠበቃል፡፡ እንዲሁም ቀደም ሲል የተሻለ እርጠበት በነበራቸውና ዘር መዝራት በተጠናቀቀባቸው አካባቢዎች በመብቀል ላይ ለሚገኙ ሰብሎች የሚጠበቀው እርጥበት የተሻለ የውኃ አቅርቦት እንዲኖራቸው ስለሚያደርግ ለሰብሎቹ እድገት መልካም ሁኔታ እንደሚፈጥር ይጠበቃል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ በሚጠበቅባቸዉ ሥፍራዎች ላይ በተለይም በአንዳንድ የሰሜን ምዕራብና የመካከለኛዉ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል ስለሚችል በማሳ ላይ ዉሃ በመተኛት በቡቃያ ደረጃ ላይ በሚገኙ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ አስፈላጊው ዝግጅትና ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተለይም በመደበኛ ሁኔታ በእርጥበት መብዛት የሚታወቁ አካባቢዎች የማጠንፈፊያ ቦዮችንና የጎርፍ መከላከያ እርከኖችን አስቀድሞ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ከእርጥበት መብዛት ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ የአረም መብዛትና፤ የሰብል በሽታወችን መቆጣጠር፤ የማደበሪያና ጸረ-ተባይ ኬሚካሎችን አጠቃቀም የዝናቡን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ በጥንቃቄ ማከናዎን ያስፈልጋል፡፡ በአንፃሩ በመደበኛ ሁኔታቸው የእርጥበት እጥረት በሚያጠቃቸው አካባቢዎች በቂ ዝግጅት በማድረግ የሚገኘውን እርጥበት በሰብል ማሳዎች ላይ እንዲቆይ ማድረግና በተጨማሪም ከማሳ ውጪ የውኃ ማሰባሰብ ስራዎች ትኩረት እንዲያገኙ ይመከራል፡፡ በአንዳንድ የአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚጠበቀው አነስተኛ መጠን ያለው እርጥበት የመጠጥ ውኃ አቅርቦትንና የእጽዋት ልምላሜን እንደሚያሻሽል የሚጠበቅ ቢሆንም የሚገኘውን ውኃ በጥንቃቄ መያዝና በተለያየ መልኩ ከሚከሰት ብክነት መከላከል ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪዉ የጁላይ ወር የክረምት የእርጥበት ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በብዙዎቹ የሀገሪቱ የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ እየተጠናከሩ ሊሄዱ እንደሚችሉና ከዚህም ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል ወቅታዊውን የእርጥበት መጠን በመደበኛ ሁኔታ ማግኘት የጀመሩትን የምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ተፋሰሶችን ጨምሮ የሰሜን ምሥራቅ እና የምሥራቅ ተፋሰሶዎችን የሸፈነ የእርጥበት መጠን ከመጠበቁም በላይ በአንዳንድ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የተሻላ የእርጥበት መጠን እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህንን ሁኔታ ተከትሎ በአብዛኛው አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ስምጥሸለቆ፣ ኦሞጊቤ፣ አፋርዳናከል፣ የላይኛዉና የመካከለኛው ዋቢሸበሌ እንዲሁም ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከእረርጥበታማ እስከ ከፍተኛ እርጥበት እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በተጠቀሱት ተፋሰሶች ላይ ይህ ሁኔታ ለውሃ ሃብት መጠን መጨመር ጥሩ አስተዋፆ ቢኖረውም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የሚከሰተው ከባድ ዝናብ በገደላማ ቦታዎች ላይ መሬት መንሸራተትና እንዲሁም የወንዞች ሙላትና ለጎርፍ ተጋላጭ ተፋሰሶዎች ላይ ደግሞ ቅፅፈታዊ ጎርፍ ሊስከትል ስለሚችል በተዳፋትና ገደላማ ቦታዎች አካባቢዎች የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች እና በንብረት ጉዳት እንዳያስከትል አስፈላጊውን ቅድመ ጥንቃቅ ማድረግ ያስፈልጋል። በሌላ በኩል የታችኛዉ ገናሌዳዋ፣ ስምጥሸለቆ እንዲሁም ኦሞጊቤ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ እንደሚያገኙ ይጠበቃል።